







በከተማዋ የተገነቡ የገበያ ማዕከላት፣ የመኪና ማቆሚያዎች እና ተርሚናሎች ተመርቀው ለአገልግሎት ክፍት በተደረጉበት ወቅት ።





የ2018 በጀት ዓመት የባለድርሻ ተቋማት ቅንጅታዊ አሰራር ዕቅድ ውይይት በተካሂደበት ወቅት ።

## አጋላጭ አሰራሮችን ፈትሾ በማረም የሌብነትና ብልሹ አሰራር ተግባርና ዝንባሌን ከምንጩ ማድረቅ እንደሚገባ ተገለጸ።






ይህ የተገለፀው የቢሮው የስነ-ምግባርና ፀረ ሙስና ዳይሬክቶሬት በዛሬው ዕለት ለቢሮው አመራርና ሰራተኞች በስነ-ምግባርና ፀረ ሙስና ትግል ዙሪያ ባሰናዳው የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና መድረክ ላይ ነው። የቢሮው የስነ-ምግባርና ፀረ ሙስና ዳይሬክተር አቶ ወንድምአገኝ አበራ በስልጠናው መክፈቻ ላይ ባስተላለፉት መልዕክት ሌብነትን ቀይ መስመር አድርጎ በቁርጠኛ ተቋማዊ መርህ ተልዕኮውን እያሳካ የሚገኘው ዲዛይንና ግንባታ ስራዎች ቢሮ በዘረጋቸው በርካታ የመታገያ ስልቶች ቀደም ሲል ይነሱ የነበሩ ቅሬታና ጥቆማዎች እያሽቆለቆሉ መጥተው በ2017 በጀት ዓመት ከየትኛውም አካል ለስራ ክፍሉ ጥቆማና ቅሬታ ሳይቀርብ መጠናቀቁን በመግለፅ ይህም ተቋሙ የገነባው መልካም ስም ሁለንተናዊ መሆኑን የሚያሳይ ነው ብለዋል።

የስራ ክፍሉ ሲኒየር ባለሙያ አቶ ደበላ ጉቱ ይህን ስልጠና በሰጡበት ወቅት እንደተገለፁት አብዛኛው ሰው ካለው ግንዛቤ አንፃር ሙስናን በግዙፍ መጠን ብቻ የመለካት ልክ ያልሆነ አዝማሚያ እንደሚስተዋል አንስተው ጥቃቅን የሚመስሉና በየስራ ክፍላችን የሚስተዋሉ የአሰራር ክፍተቶች ፣ የስነ-ምግባር ግድፈቶች እንዲሁም የሀብት እና የሰዓት አጠቃቀሞች ጭምር ድምር ውጤታቸው አገልግሎቶችን በስተጓጎል ለግዙፍ ሌብነትና ብልሹ አሰራር በር መክፈት እንደሆነ ጠቁመዋል።በመጨረሻም ለተቋሙ አገልግሎት አሰጣጥ እንቅፋት የሚሆኑና ለሙስና በር የሚከፍቱ ማንኛውም ተግባራትና ዝንባሌዎችን ያስተዋለ አካል ለስራ ክፍሉ በፅሁፍ ወይም በአካል እንዲሁም በነፃ የስልክ መስመር 9426 ላይ ጥቆማ እንዲሰጥ ጥሪ ተላልፏል።



## ዛሬ በከተማችን ያስገነባናቸውን የገበያ ማዕከላት፣ የመኪና ማቆሚያዎች እና ተርሚናሎች ለአገልግሎት ክፍት አድርገናል።





አዲስ አበባ እንደ ስሟ እያበበች ለነዋሪዎቿ ምቹ ለጐብኚዎቿ ሳቢ ሆናለች።

በቀድምዋ አዲስ አበባ ይከናወኑ የነበሩ በጣት የሚቆጠሩ አለም አቀፍ ኩነቶች በመጡ ቁጥር የከተማዋን የተጎሳቆሉ ገፅታዎች ፣ የተበከሉ አካባቢዎች ፣ አንገት አስደፊ ገፅታዎች በጥቅሉ ገመናችንን ሌሎች እንዳያዩት በረጃጅም ባነር የመሸፈን ታሪክ በልጆቿ የሌት ተቀን ትጋትና በነዋሪዎቿ ትብብር ታሪክ ሆኗል ። ዛሬ ከማለዳዉ አንስቶ ከአራዳ ጀምረን፣ በሜክሲኮ ፣ በለገሀር እና ሳር ቤት የአፍሪካ ህብረት አካባቢ የከተማችንን ገፅታ ይበልጥ የሚያሻሽሉ ፣ ለወጣቶችና ሴቶች ሰፊ የስራ ዕድል የሚፈጥሩ፣ የትራፊክ ፍሰቱን እያሳለጡ ፣ የሚያዘምኑ የአካባቢዎቹን ዉበት የሚጨምሩ ፕሮጀክቶችን ከአካባቢዉ ማህበረሰብ ጋር መርቀን ለአገልግሎት ክፍት አድርገናል ። ለአብነትም አራዳ( ባሻ ወልዴ ችሎት አካባቢ) እና ፓርኪንግን እንዲሁም አፍሪካ ህብረት ጋር ዘመናዊ የገበያ ማዕከል ፣ ፓርኪንግና የህፃናት መዝናኛ ለአገልግሎት ክፍት አድርገናል ። የአፍሪካ ህብረት የገበያ ማዕከልና ፓርኪንግ የተሰራዉ ለዲፕሎማሲዉ ማህበረሰብ የተለያዩ የስጦታና የባህል መሸጫዎችን በአቅራቢያዉ እንዲያገኝ የሚያስችል ሲሆን በ28,500 m2 ላይ የተገነባ ዘመናዊ ማዕከል ነዉ፣ሁለት ቤዝመንትና ፕላዛ ፣ 250 ሱቆች እና 250 መኪኖችን በአንድ ጊዜ ማስተናገድ ይችላል ፣ በተጨማሪም የህጻናት መጫወቻ እና ማረፍያዎች 45 መጋዘንና የመጸዳጃ ክፍሎች ፣ ፋውንቴይን ፣ አምፊ ቴአትር እና ፕላዛ አሉት።



ሌላኛዉ ባሻ ወልዴ ችሎት ጋ የተሰራዉ ዘመናዊ የመኪና ማቆሚያና ገበያ ማዕከል ሲሆን፣ በተመሳሳይ ካፍቴሪያዎች ፣ሱፐርማርኬት ፣ሱቆች ፣ሬስቶራንቶች ፣ ፕላዛ እና 200 የመኪና ማቆሚያ በውስጡ የያዘ ነዉ።

ሁለቱም ማእከላት ዘመናዊ የእሳት አደጋ መቆጣጠሪያና፣ የደህንነት ካሜራ ተገጥመውለታል ፣ ለህፃናት ፣ለአቅመ ደካምችና አረጋዉያን ምቹ እና አካታች መሰረተ ልማት ነዉ። በጥቅሉ ከሜክሲኮ እስከ ለገሃር እና አፍሪካ ህብረት ዙሪያ ባሉ የተለያዩ ቦታዎች ላይ 13 የመኪና ማቆሚና 10 ተርሚናሎች እስከ 3769 ተሽከርካሪዎችን ማስተናገድ የሚችሉ የፓርኪንግ እና ተርሚናል መሰረተ ልማቶች ጭምር ይገኙበታል ። እነኚህ ለከተማችን እድገት ከፍተኛ ፋይዳ ያላቸዉ ፕሮጀክቶች በታለመላቸዉ ጊዜ እና በጀት እንዲጠናቀቁ ሌት ተቀን ለደገፋችሁ አመራሮች ፣ ባለሙያዎችና የየአካባቢዉ ማህበረሰብ ልባዊ ምስጋናዬን አቀርባለዉ ።

# የ2018 በጀት ዓመት የባለድርሻ ተቋማት ቅንጅታዊ አሰራር ዕቅድ ውይይት ተካሄደ።



**በዛሬው ዕለት የአዲስ አበባ ዲዛይንና ግንባታ ስራዎች ቢሮ የ2018 በጀት ዓመት የባለድርሻ ተቋማት ቅንጅታዊ አሰራር ዕቅድ ውይይትና የፊርማ ስነ-ስረዓት አካሂዷል።**

ከተማ አስተዳደሩ ጥላ ስር የሚገነቡ ግንባታዎችን በባለቤትነት እንዲያከናውን በዓዋጅ ስልጣን የተሰጠው የዲዛይንና ግንባታ ስራዎች ቢሮ የተቋማት ፍላጎትን መሰረት አድርጎ በሚያስገነባቸው ፕሮጀክቶች ላይ ከቅድመ ግንባታ አንስቶ እስከ ድህረ ግንባታ ድረስ ለሚገጥሙት ህጋዊና አስተዳደራዊ ጥያቄዎች እልባት በመስጠት ተልዕኮውን በስኬት ለመፈፀም ያስችለው ዘንድ በዓዋጅ ስልጣንና ኃላፊነት ከተሰጣቸው የከተማ አስተዳደሩ አስፈፃሚ ተቋማት ጋር በ2018 ዕቅዱ ላይ መክሮ የቅንጅታዊ ትስስር ፊርማ አድርጓል። በዚሁ መድረክ ላይ የቢሮው ኃላፊ ኢ/ር አያልነሽ ሐብተማርያም እንዳሉት ይህ ቅንጅታዊ ትስስር ፕሮጀክቶቻችንን በኃላፊነት ፣በመርህና በስትራቴጂ እንድንመራ መደላድል የሚፈጥር ብቻም ሳይሆን በፕሮጀክት አፈፃፀማችን ላይም እየተስተዋለ ለሚገኘው ዕመርታ ግልፅ አበርክቶ አለው ብለዋል።

> "ተቀናጅተን መስራታችን ከዚህ ቀደም በፕሮጀክት አፈፃፀም ላይ ይስተዋል የነበረውን ስብራት በድል እንድንሻገረው አስቻይ ሁኔታን የፈጠረልን አንዱ መሳሪያችን ነው።"
>
> ኢ/ር አያልነሽ ሐብተማርያም
> የአዲስ አበባ ዲዛይንና ግንባታ ስራዎች ቢሮ ኃላፊ





ኃላፊዋ አክለውም ዘርፉ ሰፊ መዋዕለ ንዋይ የሚፈስበት ከመሆኑ ጋር ተያይዞ በፕሮጀክቶች ላይ የሚፈጠሩ ክፍተቶች ሀገርን በፅኑ የሚጎዱ ከመሆናቸው አንፃር እነዚህን ክፍተቶች መሙላትና መሻገር የምንችለው እንደዚህ በቅንጅት ስንሰራ ነው ብለዋል። በመጨረሻም በ2017 በጀት ዓመት በነበረው ቅንጅት የላቀ አፈፃፀም ላስመዘገቡ ተቋማት እውቅና በመስጠት መድረኩ ተጠናቋል።





የአዲስ አበባ ዲዛይንና ግንባታ ስራዎች ቢሮ በጥራት አስገንብቶ ለአገልግሎት ዝግጁ ያደረገውና በቅርቡ በይፋ የተመረቀውን የ AU ፓርኪንግና ፕላዛ የቢሮው ኃላፊ ኢ/ር አያልነሽ ሐብተማርያም ከመዲናዋ ለተውጣጡ የሕብረተሰብ ክፍሎች ባስጎበኙበት ወቅት

ዘመኑ የደረሰባቸውን የቴክኖሎጂ መሰረተ-ልማቶችን በማካተት በ11 ሄክታር ላይ የተገነባው ይህ ፕሮጀክት ከምድር በታች 2 እና የምድር ወለል ያለው ሲሆን በውስጡም 225 ተሽከርካሪዎችን በአንድ ጊዜ ማቆም የሚያስችል ደረጃውን የጠበቀ መኪና ማቆሚያ ስፍራን ጨምሮ ለአካልና ለአዕምሮ እፎይታን የሚያጎናፅፍ መዝናኛና ማረፊያ ስፍራ ፣ ሱቆች ፣ መካዘኖች ፣ ካፊቴሪያ እንዲሁም የአካል ጉዳት ያለባቸውን ወገኖች ከግምት ያስገቡ በቂ መፀዳጃ ቤቶችንም በውስጡ እንዲይዝ ተደርጎ በጥራት የተከናወነ ነው።

## እያንዳንዱ አመራርና ሰራተኛ ለገባው ቃል ታምኖ በተሰማራበት ዘርፍ ሁሉ መልካም አስተዳደር እንዲሰፍን መስራት እንደሚገባው ተገለፀ።





የአዲስ አበባ ዲዛይንና ግንባታ ስራዎች ቢሮ ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የከንቲባ ጽ/ቤት ጋር በመተባበር ለቢሮው አመራርና ሰራተኞች በመልካም አስተዳደር እና የቅሬታ አፈታት ላይ የዓቅም ግንባታ ስልጠና ሰጥቷል።



በዚሁ ስልጠና ላይ መልካም አስተዳደር የህዝብ ጥቅምና ፍላጎት የሚገለጽበት፣ የህዝቦች ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ተሳትፎና ተጠቃሚነት የተረጋገጠበት፣ የህዝብ ጥያቄ ተገቢ ምላሽ የሚሰጥበት፣ የህግ የበላይነትና ተጠያቂነትን የሚያሰፍን እና አሳታፊ አስተዳደራዊ ሥርዓት መሆኑ ተገልጿል። ተያይዞም በመንግሥት መሥሪያ ቤት ውስጥ መልካም አስተዳደርን ለማስፈን እና ለሚያጋጥም ቅሬታና አቤቱታ አፋጣኝ ምላሽ በመስጠት፣ ስህተቶችን ለማረምና አገልግሎት አሰጣጡን ውጤታማ ማድረግ ተጨባጭ ስራዎችን ማከናወን እንደሚገባ በስልጠናው ተብራርቷል። በመጨረሻም ውጤታማ ያልሆነ የቅሬታ አፈታት ስርዓት በሀገር ላይ የኢኮኖሚ ፖሊሲ ክፍተት፤ ውጤታማ ያልሆነ ሲቪል ሰርቪስ፤የፍትህ ስርዓት አለመረጋገጥ እና መሰል የመልካም አስተዳደር ክፍተቶች ሰለሚፈጥር እነዚህን ቸግሮች ለመቅረፍ በየተቋማቱ የህግ የበላይነትን እንዲረጋገጥ ማስቻል ፤በስራዎች ላይ የጋራ መግባባትን መፍጠር፤ግልፅነት እና ተጠያቂነት ያለበት የአሰራር ስርዓት ማስፈን እንዲሁም በተከታታይነት የአመራሩን እና የፈፃሚውን ዓቅም መገንባት አስፈላጊ እንደሆነም ተጠቁሟል።



# የሰኞ የሰራተኞች የዕውቀት ሽግግር በተካሂደበት ወቅት።





የዲዛይንና ግንባታ ሥራዎች ቢሮ አመራር እና ሰራተኞች መካከል የሚካሄደው የእውቀት ሽግግር ፕሮግራም ዛሬም ተካሂዷል።

የዛሬ ፕሮግራም በኮንስትራክሽን ግብአት ጥናት እና አቅም ግንባታ ዳይሬክቶሬት ቀርቧል። አቅራቢው አቶ ገዛኸኝ ጌታቸው በአገልግሎት አሰጣጥ ዙሪያ ሳይንሳዊ ግኝቶችን ለሰራተኞች አቅርቧል። የአዲስ አበባ ከተማ ዲዛይንና ግንባታ ስራዎች ቢሮ ለተከታታይ አመታት በከተማው ቀዳሚ በመሆን ያጠናቀቀ ቢሮ እንደመሆኑ መጠን ይህን ጠንካራ የአገልግሎት አሰጣጥ እና የመፈጸም አቅም በዘላቂነት ለመገንባት እንዲያስችል በ8 ሳይንሳዊ የአገልግሎት አሰጣጥ ጥናቶች ዙሪያ እውቀቱን አስተላልፏል። በመጨረሻም ሁሉም አመራሮች እና ሰራተኞች የእለቱን የእውቀት ሽግግር አድርገው በተነቃቃ የአገልግሎት ሰጪነት እና የሥራ መንፈስ የሳምንቱን መደበኛ ስራ ጀምረዋል።





## የሰኞ የሰራተኞች የዕውቀት ሽግግር በተካሂደበት ወቅት።







የዲዛይንና ግንባታ ሥራዎች ቢሮ አመራር እና ሰራተኞች መካከል የሚካሄደው የእውቀት ሽግግር ፕሮግራም ዛሬም ተካሂዷል።

የዕለቱ ፕሮግራም ተረኛ አቅራቢ በሆነው የቢሮው ኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ዳይሬክቶሬት የተሰናዳ ሲሆን በዳይሬክተሩ አቶ እንግዱ ተሰማ ቀርቧል። በዚህም መሰረት እንደ ቢሮ የተተገበሩና አገልግሎት አሰጣጡን በማቅለል ብሎም በማሳለጥ ረገድ ታላቅ ድርሻ እየተወጡ የሚገኙ የቴክኖሎጂ ስርዓቶች ምንነት ፋይዳ እና አጠቃቀም ዙሪያ ሙያዊ ገለፃና የዕውቀት ሽግግር ተደርጓል።በመጨረሻም ሁሉም አመራሮች እና ሰራተኞች የእለቱን የእውቀት ሽግግር አድርገው በተነቃቃ የአገልግሎት ሰጪነት እና የሥራ መንፈስ የሳምንቱን መደበኛ ስራ ጀምረዋል።